# የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴዎች ከልጅዎ ጋር ስለ ሒሳብ ለመነጋገር የሚያስችሉ ግሩም አጋጣሚዎች ናቸው!

## ሒሳብ በሁሉም ቦታ አለ!




### ምግብ እያበሰሉ እያለ

- ስለ መለኪያዎች ማውራት፣ ልጅዎም እንዲረዳዎ ማድረግ ይችላሉ። «ሦስት ኩባያዎች ያስፈልጉናል። አሁን የመጀመሪያውን አስገብተናል። ስንት መጨመር ይኖርብናል?»
- የመለኪያ ኩባያዎችን መጠኖች ማወዳደር ይችላሉ።

### ልብስ እያጠቡ እያለ

- አልባሳትን ወይም የልብስ ቁልፎችን መቁጠር ይችላሉ።
- አልባሳትን በቀለም ወይም በሌላ በመረጡት ምድብ መደርደር ይችላሉ።
- ስለ መጠኖች መነጋገር እና ንጽጽሮችን ማድረግ ይችላሉ።
- የልብስ ማጠቢያ ሳሙናውን መለካት ይችላሉ።







### እንቅልፍ ለመተኛት ሲዘጋጁ

- የእጅ ጣቶችን እስከ አሥር መቁጠር ይችላሉ።
- ቁጥሮችን የያዙ መጽሐፍት ማንበብ ይችላሉ።
- በሚያነቧቸው መጻሕፍት ውስጥ ቁጥሮችን፣ ቅርጾችን እና ቅጦችን መፈለግ ይችላሉ።



### ሥራ እየሠሩ እያለ

- ልጅዎ የሚደረድራቸው የተደባለቁ ሲሪያሎች፣ መጫወቻዎች፣ ቀለማት (ክሬዮንስ)፣ ኩባያዎች፣ ጎድጓዳ ሳህኖች ወይም ኮንቴይነሮች ያሉ እቃዎች መስጠት ይችላሉ።
- ልጁ እቃዎቹን ደርድሮ ሲጨርስ እንዴት እንደተደረደሩ መጠየቅ ወይም እቃዎቹን እንዲቆጥር ማድረግ ይችላሉ።




facebook.com/CambridgeSTEAMInitiative    @CambMaSTEAM

STEAM Initiative CAMBRIDGE · MathTalk · lets talk! · CAMBRIDGE PUBLIC SCHOOLS · CAMBRIDGE PUBLIC LIBRARY · CAMBRIDGE Office of Early Childhood